# ከአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ሃላፊ ከወ/እና ጎሜዝ ጋር የተደረገ ውይይት ሪፖርት

1. ግንኙነቱ የተደረገው ሃሙስ ጁን 2 ቀን ከሰአት በኋላ ነበር። ሃላፊዋ ከጣልያን አገር ወደ ሃገራቸው ወደ ፖርቱጋል ሲሄዱ ለጥቂት ሰአታት በብረስልስ ሲልፉ ለአንድ ሰአት ተኩል ተቀብለው አነጋግረውናል። በስብሰባው የተገኘነው እኔ ህብረቱን ወክየና ሌሎች ሶስት ሰዎች በቤልጀም የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ አባላት ነበሩ። ሴትዮዋ በአውሮፓ ፓርላሜንት የሶሻሊስት ግሩፕ አባል ሲሆኑ ከዚያም በተጨማሪ የፓርላማው የልማት ኮሚሽን አባል ናቸው። እንደሚሰማው ከሆነ በዚህ በኢትዮጵያ ምርጫ ጉዳይ ባሳዩት የአመራር ችሎታ በፓርላሜንቱ አድናቆት አትርፈዋል። አስተያየትና ግምገማ ማቅረብ የጀመሩት እሳቸው ናቸው። ያነሷቸው ዋና ዋና ነጥቦች

ሀ) አሁን በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ታሪካዊ ቢሆንም "ቮላታይልና" አደገኛ ነው። ህዝቡ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚች አገር ታሪክ አማራጭ ቀርቦለት የመምረጥ እድል አግኝቷል። የምርጫውን ቀን ቀደም ብሎ በሃገሪቱ ባደረግነው ቆይታ እጅግ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ የህዝቡ እንቅስቃሴ ከእለት እለት እየተስፋፋና እየተጧጧፈ እንዴት እንደሄደ ለመታዘብ ችለናል። መንግስት በዚያን ወቅት ሚድያውን ለተቃዋሚዎች በመክፈቱ ለዚህ የህዝብ ትግል መነሳሳት ላደረገው አስተዋፅኦ ሊመሰገን ይገባል።

ለ) እርግጥ ይህ የሚድያው ከፈት ማለት በምርጫው ማግስት አክትሟል። ተቃውሟችንን ማሰማት የጀመርነው ከማግስቱ ጀምረን ነው። በዚህ አንፃር በተደጋጋሚ ከበረከትም ከመለስም ጋር ተገናኝቼ "ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ተመልሳ እንደዱሮው መሆን የምትችልበት ሁኔታ የለም። ነገሮች እንደማይመለሱ ሆነው ሙሉ በሙሉ ተቀይረዋል። በሃገሩ የሚሆነውን ሁኔታ ህዝቡ በቢቢሲና በሲኤን ኤን ለመከታተል መገደዱ ፈፅሞ ትክክለኛ አካሄድ አይደለም" በማለት ደጋግመው ተቃውሞ ማሰማታቸውን ገልፀዋል። ወደፊትም በዚህ በሚድያ ጉዳይ ያለው ተቃውሞ በግልፅና እንዲያውም ከአስፈለገ እየሰፋ በሚሄድ መልክ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ሐ) ምርጫውን በተመለከተ በግልፅ ያሰሙን ነገር "ተጭበርብሯል" የሚል አስተያየት ነው። እርግጥ እንደማንኛውም ባእዳን ኢህአዴግ ከከተማ ይልቅ በገጠር ድጋፍ አለው የሚል ሃሳብ አላቸው። ቢሆንም ደግሞ አንድ በግልፅ ያስቀመጡት ነገር አለ። ይህም "ከከተማ የተሻለ ድጋፍ" አለው ሊባል ቢቻልም በሳቸው አስተያየት ኢህአዴግ እንደከተሞች በማያወላዳ ሁኔታ ባይሆን እንኳን በገጠርም ተሸንፏል የሚል ግልፅ አቋም አንፀባርቀዋል። ይህንን ሃሳባቸውን ለማስደገፍ የተጠቀሙት ቀደም ብለው ለናሙናነት 450 የምርጫ ጣቢያዎች መርጠው ስለነበረ ከዚያ በተገኘው ውጤት ላይ ተመርኩዘው እንደሆነ ተናግረዋል። ይህንንም ኢህአዴግ በገጠርም በከተማም ተሸንፏል የሚል ግምገማችንን በቀጥታም ባይሆን ለመለስም እንዲገባው አድርጌ ነግሬዋለሁ ካሉ በኋላ በዚህ በኩል ያላቸውን አስተሳሰብ ሲያጠቃልሉ "Meles knows that we know" ብለዋል። ለበረከትም በተደጋጋሚ ያልኩት የአውሮዳ ህብረት ብቻ ሳይሆን የኔም የራሴም ክሬዲቢሊቲ ጉዳይ ነው። ነገሩን ተከታትለን የደረስንበትን ሁሉ ያለ አንዳች ዲፕሎማሲ ይፋ እናደርጋለን ብየዋለሁ። manipulation የሚኖር ከሆነ አይኔን እንድዘጋ "ኤክስፔክት" አታድርግ ብየዋለሁ።

መ) ስለምርጫው ውጤት እሳቸውም ሆኑ የታዛቢዎቹ ቡድን አባላት ያላቸው አስተሳሰብ ይህንን ውጤት ኢህአዴግም፤ ተቃዋሚዎችም "still less" አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ጨርሶ የጠበቁት ነገር አልነበረም የሚል ነው። "It was a shock to both sides." በተለይ መለስ ከየአቅጣጫው የተሳሳቱ መረጃዎች ስለሚጎርፉለት ስላለው ሁኔታ ትክክለኛ ስእል አልነበረውም። ይህንን ራሴ በተደጋጋሚ "የተሳሳተ መረጃ feed እየተደረገህ ነው" ብየ ነግሬዋለሁ።

ሠ) አሁን ያለው ሁኔታ በጣም በቋፍ ያለ ሁኔታ ነው። Any thing can derail the situation. ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ ውስጥ ላሉት አክራሪዎች በአመፅ ለመሰማራት የሚያስችላቸው ምንም አይነት ሰበብ እንዳይሰጡ በጣም መጠንቀቅ አለባቸው። If I were the opposition statesmanship አሳያለሁ። የሰከነ ሽግግር ለማድረግ ከተፈለገ ኢህአዴግንም የሚጨምር የጥምር መንግስት ለመመስረት ጥሪ ማቅረብ አለባችሁ። የፈለጋችሁትን ስም ስጡት National Unity gov. ; Gov. for national salvation etc

ረ) በተለይ በተቃዋሚዎች ላይ ኢህአዴግ የሚያካሂደው ቅስቀሳ ለአመፅና ከዚያም አልፎ ለጄኖሳይድ

እየተዘጋጁ ያሉ አክራሪዎች ናቸው የሚል ሃይለኛ ቅስቀሳ ነው። ደግመው ደጋግመው ዋሽንግተን ጉባኤ ላይ የአመፅ ስትራቴጂ ፀድቋል ይላሉ። ይህ ስትራቴጂ በዶ/ር ነገደ የተጠነሰሰ ነው እያለ በረከት መፅሃፉን እየገለጠ በተደጋጋሚ እየተረጎመ አንብቦልናል። ይህንን ለሁሉም ባአዳን ታዛቢዎች በደንብ አርጎ ያብራራ ስለሆነ ተቃዋሚዎች የአመፅ ሳይሆን ሰላማዊ፤ ህጋዊና "ማንንም የማያገልል" አቋም እንዳላቸው ለማሳየት ኢኒሸቲቭ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። ዞር ዞሮ ያለውን "ዴድሎክ" ለመስበር አንዱ ወገን "ኢንሸቲቭ" መውሰድ ስላለበት እናንተ ብትቀድሙ ለኢሜጃችሁ ጥሩ ነው።

ለ) በዚህ በኩል ለውጥ ሊያመጣ የሚችለውና ከሁሉም የኢህአዴግ መሪዎች ፍላጎቱ ያለው መለስ ነው። በአሁኑ ጊዜ በግንባሩ ውስጥ ብዙ ተቃውሞ አለበት። ግን በተደጋጋሚ ከተቃዋሚዎች ጋር ዲያሎግ እንደሚፈልግ በግልፅ ነግሮኛል። እንዲያውም በምርጫው ውጤት አጣሪ ኮሚሽን ውስጥ የግድ መግባት ይኖርባችኋል ብሎ ደጋግሞ ጠይቆናል። Don't count on Bereket and Seyoum. ከነሱ ምንም መጠበቅ አይቻልም። መለስ ግን እነ ብሌርን ጨምሮ በውጭ ብዙ ወዳጆች አሉት። በሚሰራው ሁሉ ይህንን into account ይወስዳል። ዋናው ነገር ግን ከእናንተ ግል-ፅ የሆነ "የድያሎግና የኮምፕሮማይዝ" ጥሪና የጋራ መንግስት ጥሪ በቅድሚያ መምጣት ይኖርበታል ብየ እገምታለሁ።

ሸ) እኔ ላረጋግጥላችሁ የምሻው ነገር አንደኛ እኛ የምንሰራው ከህብረቱ መንግስታት ነፃ ሆነን ነው። ሁለተኛ ምርጫውን ታዝበን ግምገማችንን ስናጠናቅቅ ከወዲሁ ማለት የምንችለው ነገር ም-ንም ማኒፑሌትድ የሆነ ነገር ካለ "We are not going to give an OK to something manipulated" ሶስተኛ ነገር ሃገሪቱን ካለችበት ቀውስ ለማውጣት በርካታና የተለያዩ መፍትሄዎች አሉ ተቃዋሚዎች ከኢህአዴግ ጋር ለመወያየት ያላቸውን ፈቃደኛነት ይፋ አድርገው በውይይት አንዱን መፍትሄ መምረጥ ይኖርባቸዋል።

ቀ) አሁን ባለው ሁኔታ ቀጣዩ ተግባር ከያለበት የመጡትን አቤቱታዎች በአጣሪው ኮሚቴ አማካኝነት ማጣራትና ውሳኔ መስጠት ነው። በኛ በኩል ያለን አቋም "We are not going to investigate but we will observe the investigation" የሚል አቋም ነው። ለዚህ ስራ እንዲረዱን ከዛው ከአዲስ አበባ የህግ ሙያተኞች በኤክስፐርትነት ቀጥረናል። ከወዲሁ ማለት የሚቻለው በተወሰኑ ወረዳዎች የተደረገው ማጭበርበር ግልፅ ስለሆነ እነዚህ ቦታዎች ምርጫው መደገሙ አይቀርም። አንዳንድ ቦታዎች ግን ጭብርብሩን በተጨባጭ ማስረጃ ለማሳየት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ለማንኛውም ውጤቱ በJune 8 ይፋ የሚሆን ከሆነ በዋዜማው አዲስ አበባ እሄዳለሁ። ከዚያ ደግሞ በሱማሌ ክልል ለሚደረገው ምርጫ በነሃሴ ወር ተመልሼ እሄዳለሁ።

በ) በመጨረሻ የምመክራችሁ በተለይ ዲያስፖራ ያላችሁት ህዝባችሁን በመደገፍና ሰላማዊ ትግል የማራመድ አላማ እንዳላችሁ እየጠቀሳችሁ በጣም መንቀሳቀስ አለባችሁ። ደብዳቤዎች ለሁሉም ፃፉ። ለኮፊ አናን፤ ለሶሎና (የአውሮፓ ህብረት የውጭ ጉዳይ ሃላፊ) ለነጆርጅ ቡሽ ለብሌር ወዘተ

3.. በኛ በኩል የተሰነዘሩት ሃሳቦችና አስተያየቶች

ሀ) መጀመሪያ ብረስልስ ባደረጉት የጥቂት ሰአታት ቆይታ በአጭር ጊዜ ጥያቄ ሊቀበሉን በመቻላው ምስጋና አቅርበናል። ከዚያም እሳው እንዳሉት ሃገራችን አንድ ታሪካዊ የሆነ የሽግግር ወቅት ላይ እንደሆነች ይህ ደግሞ ተስፋ ሰጭም አደጋ አዘልም የሆነ ሁኔታ እንደሆነ ጠንቅቀን እንደምንገነዘብ ገልፀናል።

ለ) አመፅ በሚባለው ነገር። የተቃውሞው እንቅስቃሴ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ማእበል እንደሆነና ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር አጀንዳውን ለማራመድ ሃይልና አመፅ የሚያስፈልጋቸው የኢህአዴግ መሪዎች እንጂ በምንም ስሌት ቢኬድ የዴሞክራሲያዊው እንቅስቃሴ መሪዎችና አራማጆች ሊሆኑ አይችሉም። "ጄኖሳይድ" የተባለው ነገር ክፍለ ዘመናትን ባስቆጠረው የሃገራችን ታሪክ ፈፅሞ የታየ ክስተት አይደለም። ይህ የነአቶ መለስ ውንጀላ እናንተን ሊያስደነግጥ ቢችል እኛን ደግሞ አሳፍሮናል። ከታሪክ ብቻ ሳይሆን እናንተ እዛው እያላችሁ ለምሳሌ አዲስ አበባ ከሁለት ሚልዮን ህዝብ በላይ ሰልፍ ሲወጣ ምንም አይነት ችግር አለመፈጠሩና አንድም ፀረ ትግራይ ስሜት እንደሌለ፤ ህዝባዊው እንቅስቃሴ ሰላም እንደሚፈልግና በሰላምም እ-ንደሚካሄድ አይታችኋል። ለማንኛውም አሁን ባለው ሁኔታ ያልጠበቁት ሽንፈት ያጋጠማቸው የኢህአዴግ መሪዎች ተቃዋሚዎችን የአመፅ ሴራ በመጠንሰስ

ሲወነጅሉ እናንተ ያለውን ሃቅ በደንብ የተረዳችሁት ይመስለናል። ስለዚህ በአጠቃላይ አለም አቀፉ ኮሙኒቲ የምንጠይቀው "ነገሩን ጠንቅቀን እናውቃለን፤ ከህዝቡም ሆነ ከተቃዋሚ ድርጅቶች እንኳን የጄኖሲድ የተራ አመፅም ሴራም አደጋም የለም። ይህ አይነት ነገር ቢከሰት ማን እንደቀሰቀሰው በጥብቅ እንከታተላለን" ብላችሁ ለኢህአዴግ መሪዎች ማስጠንቀቂያ ማበራከት አለባችሁ።

ሐ) ከኢህአዴግ ጋር ውይይትና እንዲያውም የጋራ መንግስት ስለተባለው። አሁን ያለው ሁኔታ ህዝባችን ተሰውቶ፤ ይህ ነው የማይባል 'ሪስክ" ወስዶ ድምፅ ሰጥቶ ከዳር እስከ ዳር የሚገኝበት "ሙድ" ለእናንተም ግልፅ ይመስለናል። ህዝቡ ኢህአዴግ ተሸንፏል ብሎ ያምናል። በዚህ ሁኔታ ኢህአዴግ አሸነፍኩ ቢል በማጭበርበርና ድምፄን በመቀማት ብቻ ነው የሚል ምንም ሊነቀንቀው የማይችል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ዋናው ቁም ነገር ከኢህአዴግ ጋር ውይይት፤ የጋራ መንግስት ወዘተ የሚለው ጥያቄ አይደለም።

መጀመሪያ የምርጫው ውጤት ጉዳይ ህጋዊ የሆነና በህዝባችን ፊት ተአማኒነት ያለው እልባት ማግኘት አለበት። በተቃዋሚዎች በኩል ሁለት መቶ በሚጠጉ ወረዳዎች ኢህአዴግ አሸነፍኩ ያለው አጭበርብሮ ነው የሚል ክስ ተመስርቷል። ለዚህም ማስረጃዎች ቀርበዋል። ህዝቡ የነዚህን አቤቱታዎች ውጤት በጉጉትና በተስፋ እየጠበቀ ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች እንደጠየቁትና ኢህአዴግም እንደተስማማበት አሁን አጣሪ ኮሚቴ እየተቋቋመ ነው። የአለም አቀፍ ታዛቢዎች በዚህ ኮሚቴ ውስጥ መገኘት ወሳኝ ጥያቄ ነው። እነሱም ባሉበት አቤቱታዎቹ ይጣሩ። ለኛና በተለይም ደግሞ ለህዝባችን ዋናው ቁምነገር ጉዳዩ በዚህ ህጋዊ ሂደት መቋጠሩ ነው።

ሁለተኛ ከዚያ በኋላ ስለዲያሎግም ሆነ ከዚያም አልፎ እርስዎ ስላነሱት የጋራ መንግስት ጉዳይ መወያየት ይቻላል። የምርጫው ሃቀኛ ውጤት ከተረጋገጠ በኋላ ብቻ ነው ኢህአዴግም ሆነ ተቃዋሚዎች በሃቅ እንዳገኙት መቀመጫና ክብደት መደራደር የሚችሉት። ይህ ኖርማል የሆነ የዴሞክራሲ አካሄድ ነው። ይህ የምርጫ ሂደት ህጋዊ በሆነ ዘዴ እስካልተቋጠረ ድረስ አንዳንድ ባእዳን ወዳጆቻችን ባለፈው ጊዜ 12 መቀመጫ ነበራችሁ አሁን ሁለት መቶ ደርሳችሁዋል፤ ይህንን ተቀብላችሁ የሚቀጥለውን ምርጫ ጠብቁ የሚሉን የሚሰራ አይደለም። ዛሬ በስንት መስዋእትነት ድል አደረግሁ ብሎ የሚያምንን ህዝብ "ተጭበርብሩዋል ግን ግድ የለም እንለፈውና ለሚቀጥለው እንዘጋጅ" ካልነው ከፖለቲካም ከሞራልም አንፃር ልክ አይሆንም። ህዝባችን እንደክህደት ነው የሚቆጥረው። ህዝቡ በምርጫ ሂደት እምነት ሊያጣ ይችላል። ይህ ደግሞ ትልቅ ችግር እንደሚያስከትል መጠራጠር አይቻልምበማለት አስረድተናል።

## አስተያየትና ማሳሰቢያ

አሁን ባለው ሁኔታ አለም አቀፍ ታዛቢዎችም ሆኑ በጠቅላላው አለም አቀፉ ኮሙኒቲ በአንድ በኩል በተቃዋሚዎች በኩል የአመፅ ሴራ እንደሌለ በሚገባ ያውቃል። በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ ተሸንፏል የሚለው አስተሳሰብ ቀስ በቀስ እየሰረፀና አሸነፍኩ ቢል በማጭበርበር ብቻ እንደሚሆን ለብዙዎች ግልፅ እየሆነ ነው። የዚያኑ ያህል ደግሞ አንድ ሁኔታውን የሚከታተል ባእድ እንዳለኝ ስልጣን ለመልቀቅ የማይፈልግ ወይም ያልተዘጋጀ ሃይል ስለሆነ በተለይ አለም አቀፉ ኮሙኒቲ "ተጭበርብሩዋል" የሚል አቋም ካስተጋባ በኢህአዴግ በኩል "Cornered cat reaction" ሊኖር ይችላል የሚል ፍራቻ አለ። የተቃዋሚው ወገን (ቅንጅቱም ሆነ ህብረቱ) አንዱ ፖለቲካው የብሄራዊ እርቅ ፖሊቲካ እንደሆነ ለማሳየት ሰፊ ዘመቻ ያስፈልጋል። ለዚህ ምናልባት ጠቃሚ የሚሆነው ከህብረቱ ፕሮግራም ስለ ዴሞክራታይዜሽንና ስለ ብሄራዊ እርቅ የሚያወራውን ክፍል ባስቸኳይ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ በዚያ ዙሪያ ሰፊ ቅስቀሳ ማድረግ አስፈላጊ ይመስለኛል። ቢበዛ 10 ገፅ ስለሚሆን አንድ ሁለት ሰው ተጋግዞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያደርሰው ይችላል።

በውይይቱ ወቅት በተደጋጋሚ "ይህንን የምለው off the record ነው፤ ይህንን አስተያየት የምሰጠው እንደ ቡድን መሪ ሳይሆን በራሴ ስም ነው" እያሉ ስለነበረ ይህንን ሪፖርት ለራሳችን የውስጥ ግምገማ እንጂ በይፋ አውጥተን ብንጠቀምበት የወደፊቱን ግንኙነታችንን ሊያሻክር ስለሚችል ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስባለሁ

ነገደ 04/06/05